# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 1 ቁጥር 30 የካቲት 6 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

# ፍትህ እና ማኅበራዊ ፍትህ



# ‹‹ኢዜማ ሶስቱን የተወካዮች ም/ቤት መቀመጫ ብቻ ሳይሆን 155ቱን የክልሉን ም/ቤት ወንበር ሊያሸንፍ የሚችልበት እድል አለ›› ብዙነሕ ፅጌ

የካቲት 6 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ቅዳሜ ጥር 30 ቀን 2012 ዓ.ም በጋምቤላ ክልል ለሚገኙ አባላት በጋምቤላ ከተማ ሥልጠና ሰጠ፡፡

ሥልጠናው መስጠት ያስፈለገው በጋምቤላ አካባቢ ያለውን የፓርቲውን መዋቅር በበለጠ አጠናክሮ ድርጅታዊ ሥራውን ወደተሻለ ቦታ ለማድረስ መሆኑን ስልጠናውን ለመስጠት ወደ ጋምቤላ ያቀኑት ብዙነሕ ፅጌ ለዜጎች መድረክ ገልፀዋል፡፡

የኢዜማ መሰረታዊ ግንዛቤዎች ምንድን ናቸው? የኢዜማ ራዕይ፣ግብ፣ ተልዕኮ ምንድን ናቸው? ኢዜማ የሚከተለው የዜግነት ፖለቲካ እና የፖለቲካ ፍልስፍና የሆነው ማኅበራዊ ፍትህ ምንድን ነው? የኢዜማ ሕገ ደንብ እና መዋቅሮቹ የተሰሩበት መሰረታዊ መርሆች ምንድን ናቸው? በኢዜማ ሁኔታ ድርጅታዊ ባህል ምንድን ነው? የሚሉት ነጥቦች ሥልጠናው አትኩሮት ሰጥቶ የዳሰሳቸው ነጥቦች ነበሩ፡፡ በያዝነው ዓመት መጠናቀቂያ ላይ ይደረጋል ተብሎ ለሚጠበቀው ምርጫ በኢዜማ በኩል የሚደረገውን ዝግጅት በሚመለከት ከብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ጨምሮ እስከ ምርጫ ወረዳ ድረስ ያሉ የድርጅቱ አካላት በየደረጃው እያደረጉ ያሉት ዝግጅት በሚመለከት እና ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንዛቤ ማብራሪያ መሰጠቱንም ብዙነሕ ፅጌ ጠቁመዋል፡፡

ኢዜማ በጋምቤላ አካባቢ ያለውን መዋቅር በሚመለከት እንዴት እንደገመገሙት ዜጎች መድረክ ጥያቄ ያነሳላቸው ብዙነሕ ፅጌ ኢዜማ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ክልሉ ላለው ሶስቱ ወንበሮች ላይ ብቻ ሳይሆን በ14ቱም የወረዳ መስተዳድሮች ድረስ የሚዘልቅ መዋቅር መዘርጋት እንደሚኖርበትና እስካሁን ድረስ በሁለት የምርጫ ወረዳዎች ላይ እታች ድረስ በማደራጀት የተሠራው ሥራ ጥሩ ጅማሮ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የጋምቤላ ምርጫ ወረዳ እና መዥንገር ምርጫ ወረዳ ላይ ጥሩ ሥራ መሠራቱን ገልፀው በኑዌር አካባቢ ባለው ምርጫ ወረዳ ተመሳሳይ ሥራ መሠራት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡ በአጠቃላይ ግን እስካሁን ጋምቤላ ላይ የተሰራው ሥራ ተስፋ ሠጪ የሚባል መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ኢዜማ ሶስቱን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫ ብቻ ሳይሆን 155ቱን የክልሉን ምክር ቤት ወንበር ሊያሸንፍ የሚችልበት እድል እንዳለ መገንዘባቸውን ብዙነሕ ፅጌ አስረድተዋል፡፡

ክልሉን በሚመለከት ምን እንዳስተዋሉ ዜጎች መድረክ ላነሳላቸው ጥያቄም ብዙነሕ ፅጌ ሲመልሱ ‹‹እምቅ አቅም ያለበት የሀገራችን ክፍል ነው፡፡ ደሕና አስተዳደር ቢያገኝና የራሱን መሪዎች መምረጥ ቢችል ከፍተኛ ሥራ ሊሠራበት የሚችል ክልል ነው ብዩ ነው የማምነው፡፡ ሕዝቡም በኢትዮጵያዊነቱ ላይ ጥያቄ የለውም፡፡ በኢትዮጵያዊነቱ ላይ ጥያቄ የማያነሳ መሆኑ ደግሞ አሁን ላለው ሀገራዊ ችግር መፍትሄ ለመስጠት ትልቅ አስተዋፅኦ ሊያደርግ የሚችል ነው፡፡›› ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

# በአዲስ አበባ ከሚገኙ የኢዜማ የምርጫ ወረዳ ሊ.ቃነ መናብርት ጋር በምርጫ ጉዳይ ውይይት ተደረገ

የካቲት 6 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)





የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በምርጫ ስትራቴጂክና ማኔጅመንት ኮሚቴ አስተባባሪ በቀጣዩ ሀገር አቀፍ ምርጫ በአዲስ አበባ የሚደረግ የምርጫ ዘመቻ ላይ ዋና ትኩረቱን ያደረገ ውይይት የካቲት 4 ቀን 2012 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከሚገኙ የምርጫ ወረዳ ሊ.ቃነ መናብርት ጋር ተካሄደ፡፡

በውይይቱ ላይ የተሳተፉ ሊ.ቃነ መናብርት ምርጫን በተመለከተ መነሳት አለባቸው የሚሏቸውን ጥያቄዎችና አስተያየቶች ሰንዝረዋል፡፡ ከተነሱት መካከል፡- የእጩ መመዘኛዎች ጸድቀው ከመተግበራቸው በፊት ወረዳዎችን መወያየት ነበረባቸው የሚል ተነስቶ ካለው ጊዜ አንጻር ሥራዎች በአስቸኳይ መሠራት ስላለባቸው ማወያየት እንዳልተቻለ ነገር ግን አሁንም ቢሆን በቀረበው መስፈርት ላይ የሚነሳና አሳማኝ የሆነ ነገር ከቀረበ መሻሻል እንደሚችል እና ዝግ እንዳልሆነ ተብራርቷል፡፡ የምርጫ ወረዳ ሊቀ መንበር፣ ምክትል ሊቀ መንበር እና ጸሐፊ ምርጫ እንደማይወዳደር በኢዜማ ደንብ ላይ በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን የአስመራጆች ሥራን ግልጽነት ባለው መልኩ እንዲካሄድ ስለታሰበ በእጩ አስመራጭነት ከሚዋቀሩት 5 አባላት መካከል የምርጫ ወረዳ ሊቀመንር እና ዋና ጸሐፊ በአባልነት እዲሳተፉ ነገር ግን የኮሚቴው ሰብሳቢ የሚሆነው/ የምትሆነው ከወረዳ ሊቀመንርና ከጸሐፊ ውጭ እንዲሆን መደረጉ ታውቋል፡፡

በቀጣይም አዲስ አበባ ላይ ትኩረቱን የሚያደርግ የምርጫ ሂደትን የሚከታተል ኮሚቴ እንደሚዋቀር፣ በሳምንት አንድ ቀንም ምርጫውን በተመለከተ ከኢዜማ መሪ ጋር ስብሰባ እንደሚኖር የፓርቲውን የዕለት ተዕለት ሥራ በኢዜማ ሊቀመንበር በኩል እንደሚከናወን ታውቋል፡፡

በኢዜማ መመሪያና ደንብ መሠረት የፓርቲው ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበርና ዋና ጸሐፊን እንዲሁም የምርጫ ወረዳ ሊ.ቃነ መናብርትና ጸሐፊዎች በሀገር አቀፍ ምርጫ ላይ መሳተፍ እንደማይችሉ የሚደነገግ ቢሆንም ምርጫ ለመወዳደር እጩ ሆኖ ከሚቀርበው በላይ በምርጫው ላይ ትልቅ ኃላፊነትና ሚና እንዳለባቸው እና ተጨባጭ የሆነ ሥራ ሊሠራ የሚችለው በእነሱ በኩል መሆኑም ተገልጿል፡፡ የኢዜማ የምርጫ ወረዳ ሥራ አስፈጻሚዎች የመንግሥት እና የፓርቲ ኃላፊነትን በግልጽ በለየ አደረጃጀት እና መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ዕጩ ሆነው መቅረብ አይችሉም፡፡ ነገር ግን በየምርጫ ወረዳዎቹ በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ በብቃታቸው እና ሥነምግባራቸው የተመሰከረላቸውን ዜጎች የመመልመል፣ በኢዜማ መርሆዎች ማነጽ እንዲሁም እጩ ሆነው የሚቀርቡት አባሎች በምርጫው ማሸነፍ እዲችሉ ሙሉ ድጋፍ እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ቀጣዩ ምርጫ የወጣለት የጊዜ ሰሌዳን መሠረት በማድረግ ሁሉ አቀፍ ዝግጅት እያደረገ ያለው ኢዜማ እስካሁን በአባልነት ያልተመዘገቡ እና በምርጫ መወዳደር የሚፈልጉ ዜግነትን መሠረት ያደረገ ፖለቲካ እና ማኅበራዊ ፍትህ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰፍን የሚፈልጉ ዜጎች በሚኖሩበት አካባቢ በሚገኙ የኢዜማ የምርጫ ወረዳዎች ሄደው በአባልነት በመመዝገብ በመስፈርቱ መሰረት ለዕጩነት መወዳደር እንደሚችሉ ጥሪ ማስተላለፉ ይወሳል፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

የካቲት 6 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ፍትህ እና ማኅበራዊ ፍትህ

የካቲት 12 ቀን የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የማህበራዊ ፍትህ ቀንን አስመልክቶ በድጋሚ የቀረበ።

## 1.መንደርደሪያ

ፍትህ ሰዎች ተዛዝነው፣ ተሳስበው እና ተረዳድተው እንዲኖሩ የሚያደርግ የበጎ ሥነ-ምግባር መርሆች ስብስብ ነው። የሰዎች ማኅበር ማለትም “ማኅበረሰብ” ከእንስሳት ማኅበር የሚለየው “በጎ” እና “በጎ ያልሆኑ”፤ “ተቀባይነት ያላቸው”፤ “ተቀባይነት የሌላቸው” እና “ሚዛናዊ የሆኑ” እና “ሚዛናዊነት የጎደላቸው” አሠራሮች የሚለዩበት ድንበር መኖሩ ነው። ይህ ድንበር ስላለ እንደማኅበረሰቡ ወግና ባህል ፍትሀዊ የሆኑ ነገሮችን ፍትሀዊ ካልሆኑ ነገሮች መለየት ይቻላል።

ማኅበራዊ ኑሯቸውን በሚያስደንቅ ሥርዓት አደራጅተው የሚኖሩ እንስሳት ያሉ ቢሆንም በእውቀ (consciously) ሊለወጥ የሚችል ሥርዓት ያለው ፍጡር ሰው ብቻ ነው። ለምሳሌ፣ የጉንዳን ሠራዊት ሰልፍ አሳምሮ ይጓዛል፤ ተጋግዞ ጠንካራ መኖሪያ ይገነባል፤ ስንቅ ያከማቻል፤ ያከፋፍላል፤ የሠራዊቱ አባል የሆነ እያንዳንዱ ጉንዳን የሚያበረክተው አስተዋጽዖ አለው። ይሁን እንጂ ይህ የሚሆነው ግን በእውቀ በተገነባ ሥርዓት ሳይሆን ተፈጥሮ በቋሚነት በሰጠቻቸው የሥራ ድልድል መሠረት ነው። ማን “አዛዥ” ማን ደግሞ “ታዛዥ”፤ ማን አጥቂ ማን ተከላካይ እንደሚሆን በተፈጥሮዓቸው የተወሰነና የማይለወጥ ነው። የንብ መንጋም እንደዚሁ ነው፤ አንዷ ለንግሥትነትና እናትነት፤ ከፊሎች ለአውራነት፤ ከፊሉ ለጥበቃ፤ በርከት ያሉት ለአገልጋይነት ተፈጥረዋል፤ ይህንን ተፈጥሮ ሊቀይሩት ቀርቶ ሊያሻሽሉት እንኳን አይችሉም። ተፈጥሮዓቸው በመሆኑ ይህ ዓይነቱ የኃላፊነት ድልድል ፍትሀዊም፣ ኢፍትሀዊ ተብሎ ሊመደብ አይችልም።

ሰው በማኅበር ሲኖር ግን ራሱን ያደራጀው ከተፈጥሮ አውድ ወጥቶ ነው። ሰው ሲፈጠር ጥቂቶች ለመሪነት፣ ብዙዎች ለተመሪነት ተብለው አልተፈጠሩም። ተፈጥሮ ከፊሉን ጭሰኛ፤ ከፊሉን ገንበኛ፣ ከፊሉን አናጢ፣ ከፊሉ ነጋዴ አድርጋ አልፈጠረችውም። ተፈጥሮ የተወሰኑ የሰው ዓይነቶችን ለሀብታምነት፣ የተቀሩትን ደግሞ ለድህነት አልፈጠረችም። ይህ ሁሉ የሆነው ሰው በፈጠረው ማኅበራዊ መስተጋብር ነው። መስተጋብሩ በአብዛኛው ሰው ተቀባይነት ካለው እና ሚዛናዊ ከሆነ “ፍትሀዊ” ነው ብለን አዎንታዊ እውቀና እንሰጠዋለን በዚሁ እንዲቀጥል እንጥራለን፤ ያ ካልሆነ ደግሞ “ኢፍትሀዊ” ነው ብለን እንኮንነዋለን፤ እንዲቀየርም እንታገላለን። የፍትህ እሳቤ ሰውኛ እሳቤ የሆነው ተፈጥሮ ከሰጠችው ውጭ ራሱን የሚደለድለው ሰው በመሆኑ ነው፤ ከሰው ዘር ውጭ የፍትህ ጉዳይ የሚያሳስባቸው ፍጥረቶች ስለመኖራቸው እስካሁን መረጃ የለም።

ምንም ዓይነት ፍትህ የሌለበት ማኅበረሰብን ለማሰብ ብንሞክር በአፅምሮዓችን ሊመጣልን የሚችለው እያንዳንዱ ግለሰብ ወይም በዝምድና የተሳሰረ ስብስብ የገዛ ራሱን ወይም ቡድኑን ለማኖርና ከጥቃት ለማዳን የሚጥርበት ሥርዓት እናገኛለን። በዚህ ሥርዓት ውስጥ “የሥጋ” ዝምድና (ለምሳሌ እናትና ልጅ) ብቸኛው ማስተሳሠሪያ ይሆናል። በሌላ አነጋገር ዘር ብቸኛ የስብስቡ ማስተሳሠሪያ ይሆናል። በማኅበረ-እንስሳት ውስጥ መንጋን የሚያስተሳስረው በዘር መነሻነት የተፈጠረ አብሮ ውሎ ማደር ነው። ፍትህ በሌለበት ማኅበረሰብም ውስጥ የሚዛመዱ ቤተሰቦች ራሳቸው በተለያየ ስያሜ ወደሚጠሩ ስብስቦች ማደግ ይችላሉ። ትልቅም ይሁኑ ትንሽ፣ ስብስቦቹን የሚያገናኛቸው ዝርያቸው ነው። የእንስሳት መንጋ በውስጡ እያንዳንዱ የራሱን ዘርን ለማቆየት በሚያደርገው የደመነፍስ ትግል ውስጥ የሚጠመድ ቢሆንም፣መንጋ በጋራ ደግሞ ለምግብና ለቦታ ከሌሎች መንጋዎች ጋር በማያቋርጥ ትንንቅ ይኖራል። በማኅበረ-እንስሳት ደካማው ብቻ ሳይሆን ጠንካራው መንጋም ቢሆን ከሱ የባሰ ጠንካራ መንጋ እንዳይመጣበት እንደሰጋ ይኖራል።

ፍትህ የሌለበት ማኅበረሰብም እንደዚያው ነው። ፍትህ በሌለበት፣ ሰዎች በዘር መደራጀታቸው ተፈጥሮዓዊ የመሆኑን በኑሮ እድሎች (opportunities) እና ግብዓቶች (resources) ላይ መጣላታቸውም እንደዝያው የማይቀር ተፈጥሮዓዊ ነው። በቡድኖች መካከል ያለው ጦርነት በአንዱ ቡድን ጊዜያዊ አሸናፊነት ጋብ ሲል በቡድኑ ውስጥ ባሉ ቤተሰቦች መካከል ጦርነት ይነሳል፤ ያ ጋብ ሲል ደግሞ በእያንዳንዱ ግለሰብ መካከል ይጀምራል። ሲከፋ ወገንና ጠላት ያልለየ ሁሉም ከሁሉም ጋር (all against all) ጦርነት ውስጥ ይገባል። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ነው ህገ-አራዊት የሚባለው። ፍትህ በሌለበት የሰው ልጆች ሕይወት ወደ ህገ-አራዊት ያሽቆለቁላል።

## 2.ፍትህ፣ ህግ፣ እና የህግ የበላይነት

ፍትህ፣ ህግ፣ እና የህግ የበላይነት በጥብቅ የተቆራኙ ቢሆንም የተለያዩ ጽንሰ-ሀሳቦች ናቸው። ፍትህ፣ ሰዎች ተሳስበው እና ተጋግዘው እንዲኖሩ የሚያደርግ፤ አድልዎንና ጥቃትን የሚከላከል፤ በዳይን የሚቀጣ፣ ተጠቂን የሚክስ ማኅበረሰቡ “ትክክለኛ”፣ ”ሚዛናዊ“ ወይም “በጎ” የሚላቸው ስነምግባሮች ስብስብ ነው። ፍትህ የማኅበራዊ ተቋማት ውጤት ነው። ህግ “ይህንን አድርግ፤ ያንን አታድርግ” የሚል ድንጋጌ ነው። አቅም ያለው ሁሉ የፈለገውን ህግ አውጥቶ ሊያስፈጽም ይችላል። ህግ መሣሪያ ሲሆን ፍትህ ህጉ በተግባር ላይ ሲውል የሚገኘው ውጤት ነው። ጥሩ ህግ በሥራ ላይ ከዋለ ፍትህን ያስገኛል። ጥሩ ህግ ኖሮ ሥራ ላይ ካልዋለ ህጉ መኖሩ ብቻውን ፍትህን አያስገኝም። መጥፎ ህግ ደግሞ ፍትህን ያጓድላል፤ ኢፍትሃዊነትን ያነግሳል። “የህግ የበላይነት” ሲባል በሁሉም ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ህግ አለ ማለት ነው። የህግ የበላይነት እንዲከበር ቢያንስ ሁለት ነገሮች መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

(1) ህግ፣ ፍትሃዊ ይሁንም አይሁን፣ ያለ አድልዎ በሥራ ላይ መዋል አለበት

መጥፎም ይሁን ጥሩ፣ አንድ ህግ በሁሉም

ላይ እኩል ሥራ ላይ ከዋለ የህግ የበላይነትን አንድ መሠረታዊ መሥፈርት አሟላ ማለት ይቻላል። በተለይም ህግ አስፈፃሚው በህጎቹ ራሱ የሚገዛባቸው መሆን አለመሆኑ ቁልፍ ጉዳይ ነው። ህግ አውጭው የሚያወጣቸውን ህጎች ህግ አስፈፃሚው ሲፈልግ በሥራ ላይ የሚያውላቸው፣ ሳይፈልግ ደግሞ የሚተዋቸው ከሆነ፣ የህጎቹ መኖር ለህግ የበላይነት መከበር የሚሰጠው ፋይዳ የለም።

ዛሬ አገራችን ውስጥ ያለው የህግ ችግር የመጥፎ (የኢፍትሃዊ) ህጎች መብዛት ብቻ አይደለም። ችግራችን ያለአድልዎ ተፈፃሚ የሚሆኑ ህጎች የመኖርና አለመኖር ጉዳይ ጭምርም ነው።

(2) የህጎች ፍትሃዊ መሆን አስፈላጊነት

ህግ ሁሉ ግን ወደ ፍትህ አያደርስም። ፍትህን የሚያሰፍኑ ህጎች አሉ፤ ኢፍትሃዊነትን የሚያሰፍኑ ህጎችም ሊኖሩ ይችላሉ። የህግና የፍትህ ግንኙነት ውስብስብ ነው። ለምሳሌ፣ ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ እንዲደርስ የማይፈልገውን ነገር በሌሎች ላይ አያደርስም፤ ሌሎች በሌሎች ላይ ጥቃት ሲያደርሱም አይቶ ዝም አይልም። ህሊናችን ኢፍትሃዊ ህጎችን ይፀየፋል።

## 3.ኢትዮጵያ፣ ህግና ፍትህ

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ በኩል ህግ አክባሪ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ፍትህ የተነፈገ ሕዝብ ነው። እንዴት ፍትህ የተነፈገ ሕዝብ ህግ አክባሪ ይሆናል? ይህ ለመረዳት የሚቸግር ወለፈንዲ (paradox) ቢሆንም እየኖርን ያለነው እውነት ነው። ለኢትዮጵያዊያን "በህግ አምላክ" ትልቅ ትርጉም ያለው ሀረግ ነው። ድሮ ተበዳይ በዳያን አግኝቶ "በህግ አምላክ ቁም ብዬሃለሁ" ካለው ፓሊስ እንኳን ባይኖር ምስክር ወይም ገላጋይ እስኪመጣ ድረስ "ቁም" የተባለው ሰው ባለበት ይቆም ነበር፤ አሊያም ተራ መንገደኛም ቢሆን የሁለቱን ነጠላዎች ቋጥሮ "አቆራኝቶ" አቤት ይላል። እንዲህ እያለ አንዳንዱ ንጉሥ ችሎት ዘንድ ይቀርባል። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲህ ፍትህ እየተነፈገውም "በህግ አምላክ" ላይ ተስፋ የማይቆርጥ ህገ አክባሪ ሕዝብ ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ህግ አክባሪነት በችሎቶች ደጃፎች ብቻ ሳይሆን በዘወትር ሕይወቱም የሚታይ ነው። በከተሞች ውስጥ የወርቅ ቤቶችን ግድግዳዎች ተደግፈው የሚያድሩ ድሆች ያሉት ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን አይቀርም። ጠመንጃ ይዞ "አገሬ መግቢያ መሳፈሪያ ሙሉልኝ" ወይም "ራበኝ፣ ለምሳ ተዘከሩኝ" የሚል ወታደር የነበረው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ይህ ሁሉ መልካም ባህል ዛሬ በዓይኖቻችን ሥር እየተንኮታኮተ ነው። ይህ በቀላሉ የማይገነባ ክቡር ባህል እያጣን ነው።

አሳዛኙ ነገር በዚህ ህግ አክባሪ ሕዝብ ጫንቃ ላይ የተጫኑ ገዢዎች የሕዝቡን ህግ አክባሪነት በሚመጥን መጠን ህግን አክብረው የሚያስከብሩ አለመሆናቸው ነው። በህግ አጠባበቅ ረገድ ኢትዮጵያ እየተጓዘችበት

**((ህግ ሁሉ ግን ወደ ፍትህ አያደርስም። ፍትህን የሚያሰፍኑ ህጎች አሉ፤ ኢፍትሃዊነትን የሚያሰፍኑ ህጎችም ሊኖሩ ይችላሉ። የህግና የፍትህ ግኑኝነት ውስብስብ ነው።))**

"ሰዎች ሁሉ እኩል መስተናገድ አለባቸው" የሚል ህግ ቢወጣ በግልቡ ሲታይ ችግር ያለው ባይመስልም በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ግን ፍትሃዊ ላይሆን ይችላል። አንድ የጤና ጣቢያ ለአንድ የአካል ጉዳት ላለበት ባለጉዳይ እና የአካል ጉዳት ለሌለበት ሌላ ባለጉዳይ እኩል መስተንግዶ መስጠት አለብኝ ቢል ኢፍትሃዊ ነው። ከሚሰጠው አገልግሎት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የአካል ጉዳተኛው የተለየ መስተንግዶ ሊሰጠው ይገባል። ከላይ በምሳሌነት የተጠቀሰው ዓይነት በደምሳሳው ሲታይ ችግር ያለበት የማይመስል ቀና ህግ እንኳን በሥራ ላይ በሚውልበት በፍትህ ሚዛን መታየት ይኖርበታል።

ሰው ሆነን ተፈጥረን በሰዎች ማኅበር ውስጥ በማደጋችን ብቻ የተወሰነ የፍትህ ስሜት በውስጣችን አለ። በዚህ የፍትህ ስሜት (በተለምዶ አነጋገር በህሊና ዳኝነት) የሚገዛ ወደ ዳኛ እንዲሄዱ ያደርግ ነበር። "የህግ አምላክን" ማክበር አምላክን ከማክበር ጋር እኩል ነበር። "የህግ አምላክ" መኖሩ ተገዢዎች በህጉ ተፈፃሚነት ላይ እምነት እንዲኖራቸው አድርጓል። ገዢዎችም ቢሆኑ ለዳኝነት ክብር እንዲሰጡ "የህግ አምላክ" በተወሰነ መጠንም ቢሆን አገልግሏል።

ከፍትህ አንፃር የቀደሙት ሥርዓቶች ብዙ ጉድለቶች የነበሩባቸው ቢሆንም ችሎትን እንደ አሁን መዘባበቻ ያላደረጉበት አንዱ ምክንያት ፍትህን ከመለኮታዊ ሥልጣን ጋር ማያያዛቸው ነው። ይህ እውነታ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ ከፍተኛ እምነት እንዲያድርበት አድርጓል። አንድ ባለጉዳይ በአንድ ዳኛ ቢፈረድበት "የህግ አምላክ" ስላለ በሚቀጥለው እርከን ላይ ያለው ዳኛ ዘንድ ፍትህን አገኛለሁ በሚል ለአቤቱታ ይጓዛል፤ እዚያም ባይሳካለት ወደሚቀጥለው እርከን ያለው የቁልቁለት ጉዞ አስፈሪ ነው። ኢትዮጵያ ከአንድ ገዢ መዳፍ ወደ ሌላው በተወረወረች ቁጥር ፍትህ ከቀድሞው በባሰ እየተረገጠች መጥታለች። የቅርቡን ዓመታት እንኳን በምሳሌነት ብንጠቅስ የአጼ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ኢፍትሃዊነት ያስመረራቸው ወገኖች ሥርዓቱን ታገሉት፤ በትግሉ አሸንፎ የወጣው ግን ከቀድሞው የባሰው ደርግ ሆነ። የደርግ ሥርዓት ያስመረራቸው ታገሉት፤ በትግሉ አሸንፎ የወጣው ግን ከደርግ የባሰው የኢህአዴግ አገዛዝ ሆነ። አሁን በጀመርነው ለውጥ ይህ የቁልቁለት ጉዞ ካልተሰበረ አደጋው በዚሁ ዓይነት ሊቀጥል ይችላል።

ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ የፍትህ እሳቤያችን ራሱ እያሽቆለቆለ መምጣቱ ነው። ቀድሞ፣ ከላይ እንደተገለፀው፣ ፍትህ መለኮታዊ ፀጋ ተደርጋ ትወሰድ ነበር፤ መቀመጫዋም ከአማልክት ጎን ነበር። "በህግ

አምላክ” ሲባልም የአማልክት መቀመጫ ነው ተብሎ ወደሚታሰበው ሰማይ እየታየ ነበር። ከማርክሳዊ ሌሊናዊ ርዕዮተዓለም መምጣት ጋር ፍትህ ከሰማየ ሰማያት ወርዳ መሬት ላይ ተፈጠፈጠች። ፍትህ ሰዎችን ሁሉ በእኩል ማየቷ ቀረና መደባዊ ሆነች። በዚህ አዲሱ ዕይታ መሠረት የላብአደሩ ፍትህ እና የቡርዣው ፍትህ ለየቅል ብቻ ሳይሆን ተቃራኒ ሆነው ተገኙ። ለአንዱ ፍትሃዊ የሆነ ነገር ሁሉ ለሌላው የከፋ ነው። ችጋር፣ ድንቁርና፣ ኃላቀርነት፣ የርስ በርስ መቆራቆሶች - ባጭሩ፤ በአገራችን ያሉ መጥፎ ነገሮች ሁሉ መሠረታቸው ኢፍትሃዊነት ነው። ፍትህ ሲጓደል በደል ይገነግናል፤ ምሬት ይመረቅዛል፤ በውጤቱም ማኅበረሰብ ይናጋል።

## 4.ማኅበራዊ ፍትህ

ከላይ እንደተገለፀው “ፍትህ” ሰዎች የማኅበራዊ ፍትህ መጓደልን የሚያመላክቱ ናቸው።

ማኅበራዊ ፍትህ እንዲሰፍን መታገል ማለት በተቻለ መጠን ዜጎች የሀገር ሀብትና እድሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ለመዋቅራዊ በደል ተጋልጠው የነበሩ ዜጎችን ከተጫኑባቸው በደል ማላቀቅ ማለት ነው። ይህ

**‹‹ ማኅበራዊ ፍትህ ከሚለካባቸው መስኮች ቀዳሚዎቹ የሀብት ክፍፍል፣ የአድልዖ መኖርና አለመኖር እና የክብር ጉዳዮች ናቸው።››**

ኢፍትሃዊ ሆነ። ከህወሓት አገዛዝ መምጣት ጋር ደግሞ ፍትህ መደባዊ መሆኗ ቀርቶ ዘውጋዊ ሆነች። በአዲሱ ዕይታ እያንዳንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ የየራሱ ፍትህ አለው። ትግሬው፣ አማራው፣ አሮሞው፣ አደሬው፣ ሶማሌው፣ አፋሩ፣ ሲዳማው፣ ጉራጌው .... እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ፍትህ አላቸው። የኦሮሞው ፍትህ ከትግሬውም ሆነ ከአማራው ሊለይ ይችላል። ለትግሬው ፍትሀዊ የሆነ ለአማራው ፍትሃዊ ላይሆን ይችላል።

ለምሳሌ አንዱ ክልል ፍትሀዊ ነው ብሎ በገነባው ሀውልት በሀሴት ሲጨፍር፤ ሌላው ስሜቱ ክፉኛ ሊጎዳ ይችላል፤ ሶስተኛው ደግሞ ግዴለሽ ሊሆን ይችላል። በአንድ ቋንቋ እየተነጋገርን መስማማት የቸገረንም የፍትህ እሳቤያችን ወደዚህ ደረጃ በመውረዱ ጭምርም ነው።

የፍትህ እጦት በሀገራችን ለሰነፈውና በየጊዜውም እየጨመረ ለመጣው የተበላለጠ (inequality) ሕይወት ምክንያት ሆኗል። ሚሊዮኖች የእለት ጉርስ ባጡበት አገር ውስጥ ጥቂቶች ሀብታቸውን የሚበትኑበት አጥተው ሲጨነቁ ማየት የሚያስቆጭ ነው። ይህ ተበላልጦ ከመንግሥት ስልጣን ጋር ካለ ቅርበት፣ ከብሔር፣ ከጎጥ፣ ከቋንቋና ከሀይማኖትና ጋር ሲዛመድ ደግሞ አደጋው ተባብረው፣ ተሳስበው እና ተጋግዘው እንዲኖሩ የሚያደርግ፤ አድልዎንና ጥቃትን የሚከላከል፤ በዳይን የሚቀጣ፣ ተበዳይን የሚክስ ማኅበረሰቡ “ትክክለኛ” ወይም “በጎ” የሚላቸው ስነምግባሮች ስብስብ ነው” ብለናል።

“ማኅበራዊ ፍትህ” ማለት ደግሞ በግለሰብ እና በማኅበረሰብ እንዲሁም በማኅበረሰብ ውስጥ ባለ ቡድን እና በማኅበረሰብ መካከል ያለ ግንኙነትን የሚመለከት ነው። ይህ ግንኙነት “ትክክለኛ” ወይም “ተቀባይነት” ያለው ከሆነ ማኅበረሰባዊ ፍትህ ሰፍኗል ማለት ሲቻል፤ ግንኙነቱ ትክክለኛ መስሎ ካልታየ የማኅበራዊ ፍትህ ችግር መኖሩን አመላካች ነው።

ማኅበራዊ ፍትህ ከሚለካባቸው መስኮች ቀዳሚዎቹ የሀብት ክፍፍል፣ የአድልዖ መኖርና አለመኖር እና የክብር ጉዳዮች ናቸው። ለምሳሌ አንድ ድሀ ድሀ ለመሆኑ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም እንኳን ምክንያቶቹን ሁሉ በሁለት ዋና ዋና ዘርፎች መመደብ ይቻላል። በአንደኛው ወገን ያሉ በራሱ ቁጥጥር ሥር ያሉ ምክንያቶች ሲሆኑ ስንፍና ከእነዚህ አንዱ ሊሆን ይችላል። በሌላ ወገን ደግሞ ከግለሰቡ ቁጥጥር ውጭ ያሉ ምክንያቶች ናቸው። ከእነዚህ ጥቂቶቹ ከድሀ ቤተሰብ መወለዱ፣ ጥሩ ትምህርትና የጤና አገልግሎች አለማግኘቱ ሊሆኑ ይችላሉ። ሁለተኛዎቹ ምክንያቶች ደግሞ በአካል ጉዳት ወይም በማኅበራዊ ቀውስ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ወገኖችም የዕድሉ ጠቃሚ እንዲሆኑ ልዩ ድጋፍ መስጠትንም ያጠቃልላል።

ማኅበራዊ ፍትህ በቁሳዊ ጉዳዮች ብቻ ሳይሆን ቁሳዊ ባልሆኑ ህሊናዊና ስነልቦናዊ ጉዳዮችንም ይመለከታል። ሰው በቆዳው ቀለም፣ በቁመቱ፣ በጾታው፣ በእድሜው፣ በአካል ብቃቱ፣ በጤንነቱ፣ በሀይማኖቱ፣ በቋንቋው፣ በሙያው፣ በዘሩ ወይም በሌላና እነዚህን በመሳሰሉ የማንነት መገለጫዎች ሳቢያ መድልዖ እንዳይደርስበት መከላከል የማኅበራዊ ፍትህ አብይ አጀንዳ ነው። ከላይ በተዘረዘሩት የማንነት መገለጫዎች ሳቢያ ለመድሎ ለተጋለጡ ዜጎች የተለየ ድጋፍ መስጠትም የማኅበራዊ ፍትህ አንዱ ግብ ነው። ከዚህ አልፎ አንድ ትውልድ በመጪው ትውልድ ላይ እዳ አስቀምጦ ማለፋም ማኅበራዊ ፍትህ የጎደለው አሠራር ነው። ይህ የሀብት አጠቃቀምን ብቻ ሳይሆን የአካባቢ ጥበቃንም (physical enviroment) ይመለከታል። መደብ፣ ብሔር፣ ቋንቋ፣ ክልል፣ ሀይማኖት፣ጾታ፣ ዕድሜ፣ የአካል ጉዳት እና በመሳሰሉት ምክንያቶች የሚደርሱ በደሎች መነሻ የማኅበራዊ ፍትህ ጉድለት ነው።

ማኅበራዊ ፍትህን ማስፈን ዜጎች ተፈጥሮ የሰጠቻቸውን ችሎታዎች ተጠቅመው ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውን፣ ማኅበረሰባቸውና

ሀገራቸውን ከዚያም አልፎ መላውን ዓለም ለመጥቀም ሰፊ እድል ይከፍትላቸዋል።

ማኅበራዊ ፍትህ በግለሰብ (ዜጋ) እና በኅብረተሰቡ መካከል መኖር የሚገባቸው ግንኙነቶች ሁሉ ሁለቱንም ወገን እኩል የሚመለከቱ ፍትሃዊ ግንኙነቶች መሆን አለባቸው የሚል ጽንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ እነዚህ ግንኙነቶች ደግሞ የዘፈቀደ ግንኙነቶች ሳይሆኑ የዜጎች እኩልነት የሚረጋገጠው እኩልነትን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ተደርገው የሚዋቀሩ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተቋሞች ሲኖሩ ብቻ ነው የሚል ትልቅ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ መርህ ነው፡፡

## 5.ኢዜማ እና ማኅበራዊ ፍትህ

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ የኤኮኖሚ ፕሮግራም እና ፖሊሲዎችን ይቀርፃል። ፓርቲያችን የመንግሥት የኤኮኖሚ ጣልቃገብነት ሊኖር የሚችልባቸውን ዘርፎች በመለየት በግልፅ የሚያስቀምጥ ሲሆን በማንኛውም ሁኔታ ከዜጎች ጋር መንግሥት ውድድር ውስጥ ሊገባ የሚችልበት እድል አይኖርም።"

> ‹‹በአንድ ሀገር ውስጥ ማኅበራዊ ፍትህ ሰፍኗል ማለት የሚቻለው የመንግሥት የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ የተመጣጠነ የሀብት እና ማኅበራዊ አገልግሎት ክፍፍል እንዲኖር የሚያስችሉ ሆነው ሲቀረጹ ነው፡፡››

በተግባራዊነታቸው ግልጽ በሆኑ የሃብት፣ የሥራ እና የትምህርት ዕድል ክፍፍልና በአጠቃላይ ዜጎች በሀገራቸው ጉዳይ ላይ ከሚያደርጉት ነጻ የፖለቲካ ተሳትፎ ባሻገር በኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍም በሚያደርጉት ተሳትፎና በሚያገኙት ዕድል መጠን በሚለካ ግንኙነት ነው፡፡ ዛሬ በአንዳንድ ያደጉ ሀገሮች ውስጥ ማኅበራዊ ፍትህ ብለው የሚጠሩት ብዙውን ጊዜ ግለሰቦች ማኅበራዊ ሚናቸውን መወጣት እስከቻሉ ድረስ ከማኅበረሰቡ ማግኘት የሚገባቸውን ማግኘት ይችላሉ የሚል ነገር ግን ለማግኘታቸው ምንም ዋስትና የማይሰጥና ባለው እና በሌለው መካከል ትልቅ ልዩነት የሚፈጥር ከፍትህ የራቀ ሂደት ነው፡፡ በአንድ ሀገር ውስጥ ማኅበራዊ ፍትህ ሰፍኗል ማለት የሚቻለው የመንግሥት የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ የተመጣጠነ የሀብት እና ማኅበራዊ አገልግሎት ክፍፍል እንዲኖር የሚያስችሉ ሆነው ሲቀረጹ ነው፡፡ ለማኅበራዊ ፍትህ ቅድሚያ በሚሰጡ ሀገሮች ውስጥ የግብር፣ የማኅበራዊ ዋስትና፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የማኅበራዊ አገልግሎት፣ የሠራተኞች እና የገበያ ቁጥጥር ተቋሞች እያንዳንዱ ዜጋ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኘውን ጥቅም እና ሸክም በተመጣጠነ መልኩ እንዲጋራ ማድረግ በሚችሉበት መልኩ የሚደራጁ መሰረታዊ ተቋሞች ናቸው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ማኅበራዊ ፍትህ ዜጎች እኩል ናቸው ስለተባለ ብቻ እኩል አይሆኑም፤ ፓርቲ የማኅበራዊ ፍትህ መስፈን ለሀገራችን እድገት ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ፕሮግራሙን የቀረፀ ፓርቲ ነው። ፓርቲያችን ለማኅበራዊ ፍትህ የሰጠውን ከፍተኛ ቦታ በፕሮግራሙ በዝርዝር ያስቀመጠ ቢሆንም የሚከተሉት የመግቢያ ዓረፍተ ነገሮች ለአብነት ያህል ቀርበዋል።

### 5.1. የኢዜማ የፓለቲካ ፕሮግራም መግቢያ

“የፓርቲያችን የፖለቲካ ፕሮግራም በወሳኝ መልኩ ያልተማከለ አስተዳደር (ፌዴራላዊ) ሥርዓትን መከተለን ምርጫው ያደረገ ነው። ከፍተኛው የመንግሥት ኃላፊነት በሕዝብ ቀጥታ ምርጫ የሚመረጥ ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓት እንዲሆን አበክሮ ይሰራል፡፡ ፓርቲያችን የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት በማረጋገጥ፤ ዜጎች ከማኅበራዊ ፍትህ እሳቤ የሚመነጩ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች የሚከተል ፕሮግራም ከሚገኝ ትሩፋት ተጠቃሚ ይሆናሉ ብሎ ያምናል፡፡ ፓርቲያችን ሕገ መንግሥት ማሻሻያ በሥርዓት በማድረግ፤ ዜጎች ያለተፅእኖ ተሳትፎ ያደረጉበት፣ የመንግሥትን ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ እንዲሆን በትጋት ይሠራል።”

### 5.2. የኢዜማ የኢኮኖሚ ፕሮግራም መግቢያ

"ፓርቲያችን ከሚከተለው የፖለቲካ ፍልስፍና /ማኅበራዊ ፍትህ/ ጋር የሚጣጣም ለዜጎች ኤኮኖሚያዊ ነፃነት

### 5.3. የኢዜማ የማኅበራዊ ፕሮግራም መግቢያ

"የፓርቲያችን ማኅበራዊ ፕሮግራም ዓላማ፤ ዜጎች በተበላሹ የመንግሥት ፖሊስ በመገፋት ከኤኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ እንዲርቁ የተደረጉ ብቻ ሳይሆን በዚሁ መነሻ ለከፍተኛ ማኅበራዊ ቀውስ የተዳረጉ ዜጎችን በስርዓቱ ውስጥ ለማካተት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡ ዜጎች በማኅበራዊ ዘርፍ ፓርቲያችን የሚወስዳቸውን ተጨባጭ እርምጃዎች በመጠቀም ራሳቸውን ጠቅመው ለሀገር የሚተርፉ ዜጎች ማድረግ የማኅበራዊ ፕሮግራማችን ቀዳሚ ትኩረት ነው።

የፓርቲያችን ፕሮግራም በምንም መልኩ ሥራ ጠልነት እና ድጋፍ ጠባቂነትን አያበረታታም፣ ዝርዝር ፖሊሲዎችም ይህን ታሣቢ ያደረጉ ይሆናሉ።"

# ኢዜማ በአዳማ ጽሕፈት ቤት መክፈት እንዳልቻለ ተገለጸ

የካቲት 6 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአዳማ ምርጫ ወረዳ 1 ቢሮ ለመክፈት ጥረት ቢያደርግም በገዢው ፓርቲ ውስጥ ያሉ አመራሮች እና የምክር ቤት ባለሥልጣኖች አከራዮች ላይ በሚፈጥሩት ጫና ምክንያት ጽሕፈት ቤት መክፈት እንዳልቻለ የምርጫ ወረዳው የፋይናንስ ኃላፊ ኤልያስ ኢብራሂም ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

ከዚህ ቀደም የኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) እንዲሁም ሌሎች ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት በአዳማ የኢዜማ ምርጫ ወረዳ 2 ጽሕፈት ቤት አስመርቆ ከከፈተ በኋላ የምርጫ ወረዳ 1 አመራሮች እና አባላቶች በወረዳቸው የሚከራይ ጽሕፈት ቤት እስኪያገኙ ድረስ በተደራቢነት ቢሮውን እየተገለገሉበት፣ ስብሰባም እያረጉበት ቢገኝም የምርጫ ወረዳ 2 ቢሮ አከራዮች ላይ በሚደርስ ጫና ጽሕፈት ቤቱን ልቀቁ ብለዋል፡፡

ጽሕፈት ቤት ለማግኘት ምን ዓይነት ጥረት አድርጋችኃል? በሚል ከዜጎች መድረክ ለቀረበላቸው ጥያቄ ‹‹ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ጽሕፈት ቤት ለመከራየት ተስማምተን ውል ልንፈጽም ስንል በማናውቀው ሁኔታ ይቋረጣል፡፡ በቅርብ እንኳን ምንጃር ጎዳና ላይ እንዲሁም ሣር ተራ አካባቢ ባሉ ህንጻዎች ላይ የሚከራይ ቢሮ አግኝተን በዋጋ ከተስማማን በኃላ የሚከራየው ኢዜማ ነው ሲባሉ ‹‹ለፖለቲካ ፓርቲ አናከራይም›› በማለት ከልክለውናል፡ ፡ ይሄ እየሆነ ያለው በኢዜማ ላይ ብቻ ነው፡፡ ሌሎች ፓርቲዎች ያለምንም ችግሮች ጽሕፈት ቤት ከፍተው እየተንቀሳቀሱ፣ ሥራም እየሠሩ ይገኛሉ፡፡›› በማለት ኤልያስ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በአዳማ ላይ ብዛት ያለው የኢዜማ ደጋፊ ይገኛል፡፡ በተለይ ኢዜማ በወጣቱ በኩል ሰፊ ድጋፍ አለው፡፡ እስካሁን ድረስ ጽሕፈት ቤት ለመክፈት የተለያዩ ተግዳሮቶችና ጫናዎች ቢኖሩም በአባሎቹ ላይ ግን እስካሁን ድረስ ምንም ዓይነት ችግሮች እንዳልገጠማቸው የፋይናንስ ኃላፊው ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ኢዜማ ከዚህ ቀደም የፓርቲው መሪ በተገኙበት በአዳማ ከተማ ጽሕፈት ቤት ተመርቆ ከመክፈቱም ባለፈ በአዳማ ከሚገኙ አባላት፣ ደጋፊዎችና ከከተማው ነዋሪዎች እንዲሁም የሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አባሎች ባሉበት ሕዝባዊ ውይይት ማድረጉ ይታወሳል፡፡

# ምርጫ ወረዳ 24 ለሀምሊን ፊስቱላ ሆስፒታል የቁሳቁስ ድጋፍ አደረገ

የካቲት 6 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ምርጫ ወረዳ 24 በአዲስ አበባ ከተማ ጦር ኃይሎች አካባቢ ለሚገኘው የሀምሊን ፊስቱላ ሆስፒታል የካቲት 05 ቀን 2012 ዓ.ም ቁሳቁሶችና የእውቅና ምስክር ወረቀት በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ በመገኘት አበረከተ፡፡

የምርጫ ወረዳው ሥራ አስፈጻሚ አባላት በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ በተገኙበት ወቅት የሆስፒታሉ የኮሚኒኬሽን ኦፊሰር አስቻለው ታደሰ የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ያደረጉ ሲሆን ሆስፒታሉ ከምስረታ ጀምሮ እያከናወናቸው ስለሚገኙ አጠቃላይ ሥራዎች ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ እንደ ኦፊሰሩ ገለፃ ሀምሊን ፊስቱላ ሆስፒታል በኢትዮጵያ በ1966 ዓ.ም እንደተመሰረተ እና ላለፉት 45 ዓመታት ከመላው ሀገሪቱ ለሚመጡ የፊስቱላ ተጠቂ ዜጎች ያለምንም ክፍያ በነጻ ህክምና ሲሰጥ መቆየቱን ገልጸው በአሁኑ ወቅት ሆስፒታሉ በሶስት ዋና ዋና የሥራ ዘርፎች፡- ህክምና በመስጠት፣ በመከላከል እና መልሶ በሚቋቋም ላይ አተኩሮ የአዲስ አበባውን ዋና ሕክምና እና እንክብካቤ መስጫ ጨምሮ በ5 የተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል፡፡

በማኅበረሰቡ ዘንድ በኖረ ልማድና ባህል መሰረት የፊስቱላ ተጠቂ ሴቶችን ወደ ህክምና ማዕከላት ከማምጣት ይልቅ ማኅበረሰቡ እንደ እርግማን በመቁጠር በጓዳ መደበቅን ስለሚመርጥ ታማሚዎችን ወደ ህክምና ማእከላት ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ላይ ፓርቲው ያለውን መዋቅርና ሀገር አቀፍ ተደራሽነት ከግምት በማስገባት ለማኅበረሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በተጓዳኝ እንዲሰራ ሲሉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ከኮሚኒኬሽን ኦፊሰሩ ገለፃ በመቀጠል የኢዜማ ብሔራዊ ስራ አስፈፃሚ አባል የሆኑት ኑሪ ሙደሲር ‹‹የምርጫ ወረዳው ጽሕፈት ቤት ከናንተ ጋር እንደዚህ ዓይነት ግንኙነት መፍጠሩ በጣም ነው የማመሰግነው፤ እንደዚህ ያሉ ማኅበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ነቅሶ ማውጣቱ እናመሰግናለን›› ያሉ ሲሆን በማስከተልም ‹‹ፓርቲው በሀገር ውስጥ ያለውን ተደራሽነት ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ በሚያስፈልገው ሁሉ ለመተባበር ዝግጁ ነው›› ብለዋል፡፡

በመጨረሻም ወረዳው ያዘጋጀውን የእውቅና ምስክር ወረቀትና እና ቁሳቁሶች የፓርቲው ብሔራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት ኑሪ ሙደሲር በሆስፒታሉ ኮሚኒኬሽን ኦፊሰሩ አስቻለው ታደሰ አማካኝነት ለሆስፒታሉ አበርክተዋል፡፡

# ‹‹ዕጩዎችን ለመመልመል ያወጣነው መስፈርት ኅብረተሰቡን የሚያገለግሉ አንጂ በኅብረተሰቡ የማይገለገሉ ሰዎችን ያመጣል››

**ኢዮብ መሳፍንት**

የካቲት 6 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜናች መድረክ)

የእጩዎች ምልመላ እና ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ አባል የሆኑት ኢዮብ መሳፍንት የካቲት 01 ቀን 2012 ዓ.ም እና የካቲት 02 ቀን 2012 ዓ.ም በአብዛኛው የምርጫ ወረዳዎች የዕጩ አስመራጭ ኮሚቴ ምርጫዎች መደረጋቸውን ለዜናች መድረክ ገለፁ፡፡

የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ምርጫዎች ያላደረጉ የምርጫ ወረዳዎች የካቲት 07 ቀን 2012 ዓ.ም እና የካቲት 08 ቀን 2012 ዓ.ም አስመራጭ ኮሚቴዎቻቸውን መርጠው እንደሚጨርሱ የገለፁት ኢዮብ በዕጩነት መቅረብ እንፈልጋለን የሚሉ ሰዎች ሰነዶችን ማቅረብ መጀመራቸውን አስረድተዋል፡፡ የካቲት 14 ቀን 2012 ዓ.ም እና የካቲት 15 ቀን 2012 ዓ.ም በዞን ደረጃ አስመራጮች ተሰብስበው የምርጫ ሂደቱን እንዴት እንደሚያስፈፅሙ ሥልጠና የሚሰጣቸው ሲሆን መጋቢት 6 ቀን 2012 ዓ.ም እስከ መጋቢት 13 ቀን 2012 ዓ.ም ባሉት ቀናት በየወረዳዎቹ የሚቀርቡት ዕጩዎች ተመርጠው እንደሚጨርሱ እንዲሁም ምርጫ ቦርድ እጩዎችን ዝርዝር ለመቀበል በሩን ክፍት በሚያደርግበት የመጀመሪያ ቀን ኢዜማ እጩዎችን እንደሚያስመዘግብ የኮሚቴው አባል ጠቁመዋል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ ከግንቦት 5 እስከ ግንቦት 19 ድረስ ባለው ቀን ፓርቲዎች ለቦርዱ እጩዎቻቸውን እንዲያሳውቁ ግዴታ የጣለ መሆኑን ያወሱት ኢዮብ፣ ኢዜማ ከዚህ ቀደም ብሎ ሥራውን ስለሚያጠናቅቅ ኢዜማን ወክለው እጩ ሆነው የሚቀርቡ ሰዎችን ስም ዝርዝር በመጀመሪያው ቀን ለቦርዱ ማቅረብ እንደሚችሉ አስታውቀዋል፡፡



የዕጩዎች ምልመላ እና ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴው አባል ምርጫውን ታሳቢ አድርጎ ፓርቲያቸው በምርጫው ላይ መሥራት ያለበትን ሥራዎች እየሠራ እንደሚገኝ እና በምርጫው ላይ ብቁ ተሳትፎ ለማድረግ የምርጫ ወረዳዎቻችንን በማጠናከር ላይ እየሠራ እንደሚገኝ ገልፀው፤ እጩዎችቻቸውን በተገቢው ሰዓት ለምርጫ ቦርድ ለማሳወቅ ይረዳ ዘንድ በየወረዳዎቹ የዕጩዎች ምልመላ ሥራ እየተሠራ እንዳለ ጠቁመዋል፡ ፡ እያንዳንዱ ወረዳዎች የሚያቀርቧቸውን እጩዎች የሚመርጡ መሆናቸውንና በማእከል ደረጃም ለየወረዳዎቹ ድጋፍ እየተደረገላቸው እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

ኢዜማን ወክለው የሚወዳደሩ እጩዎችን ወረዳዎች የሚመዝኑበት መስፈርቶች ተዘጋጅቶ ለእያንዳንዱ ወረዳ ይፋ መደረጉን የሚገልፁት የእጩዎች ምልመላ እና ድጋፍ

አስተባባሪ ኮሚቴው አባል ኢዮብ መሳፍንት፣ በየወረዳዎቹ አስመራጭ ኮሚቴ መመረጡን ገልፀው ባሳለፍነው ቅዳሜ ጥር 30 ቀን 2012 ዓ.ም እና የካቲት 1 ቀን 2012 ዓ.ም አስመራጭ ኮሚቴዎችን ወረዳዎች

ማዋቀራቸውን አስረድተዋል፡፡ የተቀሩት ወረዳዎችም የፊታችን ቅዳሜ የካቲት 07 ቀን 2012 ዓ.ም እና እሁድ የካቲት 08 ቀን 2012 ዓ.ም አስመራጭ ኮሚቴዎችን እንደሚያስመርጡ አስታውቀዋል፡፡

አስመራጭ ኮሚቴውን በሚመለከት የዜጎች መድረክ ላነሳላቸው ጥያቄ የኮሚቴው አባል ሲመልሱ አስመራጭ ኮሚቴው 5 አባላት ያሉት መሆኑን ጠቅሰው ሶስቱ በቀጥታ በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ መሆናቸውንና ከወረዳው ሥራ አስፈፃሚ ውጪ የሆኑ ገለልተኛ አባላት መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ከሶስቱ ውስጥም ቢያንስ አንድ ሴት መኖር እንዳለበት መደንገጉንና ይህም የተደረገው የሴቶችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ ሲባል መሆኑን አስረድተዋል፡፡ «የሴቶች ተሳትፎ ከሚረጋገጥበት ነገር አንዱ ይህ የኮታ ሲስተም ነው» ብለዋል የኮሚቴው አባል፡፡

ከሶስቱ ገለልተኛ አባሎች ውጪ ሁለቱ አባላት የወረዳው ሊቀመንበር እና ዋና ፀሐፊ መሆናቸውን የሚገልፁት ኢዮብ፣ አስመራጭ ኮሚቴ በድምሩ እነዚህን 5 አባላት የያዘ ኮሚቴ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የወረዳው ሊቀመንበር እና ዋና ጸሐፊ የገቡበት ምክንያት በሚመለከት ሲያስረዱም «ከመመዘኛ መስፈርቶች ውስጥ በዕጩነት የሚቀርቡ ሰዎች በአባልነት በቆዩበት ጊዜ ኢዜማ ውስጥ ጠንካራ ተሳትፎ ነበራቸው ወይ? በየወሩ መከፈል ያለባቸውን ክፍያ ወቅቱን ጠብቀው ይከፍላሉ ወይ? የሚሰጣቸው የሥራ ኃላፊነቶችን ትጋት ይወጣሉ ወይ? የሚሉ መመዘኛዎች ስላሉ እና እነዚህን መመዘኛዎች መሟላታቸውን በተሻለ ሊያውቁ የሚችሉት በምርጫ ወረዳው ውስጥ ያሉ የምርጫ ወረዳው ሥራ አስፈፃሚ አባላት ስለሆኑ የወረዳው ዋና ጸሐፊ እና ሊቀመንበር ማካተተ አስፈልጓል» ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ዕጩ ሆነው የሚቀርቡ ሰዎች በሚመለከት የወጣው መስፈርት በሚመለከት ላነሳንላቸው ጥያቄ ከፓርቲው ደንብ፣ ለወረዳዎች የተዘጋጀው ደንብ እና የምርጫ ሕጉን በማጣጣም መስፈርቶቹ መውጣታቸውን ገልፀዋል፡፡ «አንድ ሰው የፓርቲ አባል ብቻ ስለሆነ ለውድድር ብቁ አይሆንም፡፡ ሊያሟላቸው የሚገቡ ነጥቦች አሉ፡፡ የትምህርት መመዘኛ፣ የባህሪ መመዘኛ፣ የሥራ ትጋት መመዘኛዎች፣ የሥራ ልምድ መመዘኛዎች፣ ከዚህ ቀደም የነበረው የፖለቲካ ልምድ ከግምት ታሳቢ ይደረጋል» ሲሉ ገልፀዋል፡፡

«ከመመዘኛ መስፈርቶች ውስጥ በዕጩነት የሚቀርቡ ሰዎች በአባልነት በቆዩበት ጊዜ ኢዜማ ውስጥ ጠንካራ ተሳትፎ ነበራቸው ወይ? በየወሩ መከፈል ያለባቸውን ክፍያ ወቅቱን ጠብቀው ይከፍላሉ ወይ? የሚሰጣቸው የሥራ ኃላፊነቶችን ትጋት ይወጣሉ ወይ? የሚሉ መመዘኛዎች ስላሉ እና እነዚህን መመዘኛዎች መሟላታቸውን በተሻለ ሊያውቁ የሚችሉት በምርጫ ወረዳው ውስጥ ያሉ የምርጫ ወረዳው ሥራ አስፈፃሚ አባላት ስለሆኑ የወረዳው ዋና ጸሐፊ እና ሊቀመንበር ማካተተ አስፈልጓል»

ከመመዘኛ መስፈርቶች ውስጥ በዕጩነት የሚቀርቡ ሰዎች በአባልነት በቆዩበት ጊዜ ኢዜማ ውስጥ ጠንካራ ተሳትፎ ነበራቸው ወይ? በየወሩ መከፈል ያለባቸውን ክፍያ ወቅቱን ጠብቀው ይከፍላሉ ወይ? የሚሰጣቸው የሥራ ኃላፊነቶችን ትጋት ይወጣሉ ወይ? የሚሉ መመዘኛዎች ስላሉ እና እነዚህን መመዘኛዎች መሟላታቸውን በተሻለ ሊያውቁ የሚችሉት በምርጫ ወረዳው ውስጥ ያሉ የምርጫ ወረዳው ሥራ አስፈፃሚ አባላት ስለሆኑ የወረዳው ዋና ጸሐፊ እና ሊቀመንበር ማካተተ አስፈልጓል» እስካሁን አባል ያልሆኑ ከአሁን በኋላ ግን ኢዜማን ተቀላቅለው የኢዜማ ዕጩ ሆነው መቅረብ የሚፈልጉ ሰዎች ኢዜማን የሚቀላቀሉበት እድል አለ ወይ ካለስ በምን መልኩ ነው የኢዜማ እጩ ሆነው መቅረብ የሚችሉት? ስንል ላነሳንላቸው ጥያቄ ኢዮብ መሳፍንት ሲመልሱ ፓርቲያቸው እስካሁን ባደረገው እንቅስቃሴ መድረስ ያለበትን የኅብረተሰብ ክፍል ሁሉ ደርሷል ብለው እንደማያምኑና ከአሁን በኋላም የኢዜማ አባል መሆን ለሚፈልጉ ሰዎች ፓርቲያቸው በሩን ክፍት እንዳደረገ ገልፀዋል፡፡ «ኅብረተሰቡን በተሻለ ማገልገል የሚችል ሰው ነው ዕጩ ሆኖ መቅረብ አለበት ብለን ነው የምናምነው፡ ፡ የተሻሉ ሰዎች ኢዜማን እስከተቀላቀሉ ድረስ በዕጩነት የመቅረብ ዕድል አላቸው፡፡ ከእነሱ የሚጠበቀው በወረዳቸው ሄደው በአባልነት መመዝገብ ነው፡፡ በአባልነት ከተመዘገቡ በኋላም ለውድድር መቅረብ እንደሚፈልጉ በወረዳቸው ላለው የአስመራጭ ኮሚቴ በመግለፅ ያላቸውን ማስረጃዎች በሙሉ ለአስመራጭ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላሉ» ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ፓርቲያቸው ኢዜማም ቀድሞ የመጣ ሰው ነው ለዕጩነት መቅረብ ያለበት ብሎ እንደማያምንና የተሻሉ ሰዎች ዕጩ ሆኖ እንዲቀርቡ ፍላጎት እንዳለው ገልፀዋል፡፡ ኅብረተሰቡን ማገልገል እፈልጋለሁ የሚል ሰው ለውድድር ብቁ የሚሆንበት አሠራር ዘርግተናል ያሉት ኢዮብ መሳፍንት፣ ፓርቲያቸው ዕጩዎችን ለመመልመል ያወጣው መስፈርት «ኅብረተሰቡን የሚያገለግሉ እንጂ በኅብረተሰቡ የማይገለገሉ ሰዎችን ያመጣል» ብለው እንደሚያስቡ አስረድተዋል፡፡

በማኅበራዊ ፍትህ እና በዜግነት ፖለቲካ የሚያምኑ ሰዎች ኢዜማን ለመቀላቀል ጊዜው አልረፈደም ያሉት ኢዮብ መሳፍንት «ኢዜማ በሩ ሁሌም ክፍት ነው፡፡ በየወረዳዎቻችሁ ኢዜማን እንድትቀላቀሉ ጥሪዬን አቀርባለሁ» ሲሉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡